በጉምሩክ ኮሚሽን
የአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
CUSTOMS COMMISSION
ADDIS ABABA KALITI CUSTOMS BRANCH OFFICE
የሥራ አስኪያጅ ጽ/ቤት የውስጥ ማስታወሻ

ቁጥር፡ ስ/አ/ጽ/ቤት 118/12

ቀን: 05/09/2012 ዓ.ም

ለ፡- ለሁሉም የስራ ሂደቶች
ለ፡- ውስጥ ኦዲት ቡድን
ለ፡-ፕላንና የለውጥ ስራዎች ቡድን
ለ፡-ሴቶችና፣ወጣቶችና ህፃናት ቡድን
ለ፡-ገላን ጉምሩክ መቅረጫ ጣቢያ

ከ፡- ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት
አ.አ. ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

ፍቃዱ አማረ /ተወካይ/

ጉዳዩ፡- ኮቪድ-19 ለመከላከል የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መመሪያ ቁጥር 1/2012 ስለመላክ፤

ከጉምሩክ ኮሚሽን በቁጥር 4.0/0503/12 በቀን 03/09/2012 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የገቢዎች ሚኒስቴር በቁጥር 1/780/12 ቀን 24/082012 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የኮቪድ 19 ስርጭትን ለመከላከል የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈጸም የወጣውን ደንብ ማፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር 1/2012 ከሚያዚያ 09 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ በስራ ላይ እንዲውል የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት በቁጥር ሚም30-18/214 ሚያዚያ 10 ቀን 2012 ዓ.ም መላኩን ባሳወቀው መሠረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያዘጋጀውን መመሪያ ልኮልናል፡፡

ስለሆነም በመመሪያው ድንጋጌዎች መሰረት የኮሚሽኑ ስራዎች ወረርሽኙን በመከላከል ሂደት በአግባቡ ተፈጻሚ እንዲደረጉ እያሳሰብን፤ የኮቪድ-19 ስርጭትን ለመከላከል፤ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈጸም የወጣውን ደንብ ለማስፈጸም በሚኒስትሮች ኮሚቴ የወጣ የትራንስፖርት ዘርፍ ማስፈጸሚያ የሚኒስትሮች ኮሚቴ መመሪያ ቁጥር 1/2012ዓ.ም መሠረት እንዲፈጸም እያሳሰብኩ ለአፈጻጸም ይረዳችሁ ዘንድ የተላከው 19 ገጽ ኮፒ አባሪ በማድረግ የላክን መሆኑን አሳውቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ
ለ፡- ም/ስራ አስኪያጅ (አምራች ወጪና ሌሎች ጣቢያዎች)
ለ፡- ም/ስራ አስኪያጅ (የንግድ ገቢ ዕቃዎች ኦፕሬሽን)
ለ፡- ም/ስራ አስኪያጅ (ህግ ተገዥነት)
ለ፡- ም/ስራ አስኪያጅ(አቅምና ድጋፍ)
ለ፡- ሥነ-ምግባር መከታተያ ቡድን
አ.አ. ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገቢዎች ሚኒስቴር
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF REVENUES

ገቢ - 1021
20/8/12

ቀን ሚያዝያ 24 2012
Date
ቁጥር 1/780/12
Ref.No

ለታክስ ኦፕሬሽን ዘርፍ
ለሕግ ተገዥነት ዘርፍ
ለተቋማዊ አቅምና ድጋፍ ዘርፍ
<u>ገቢዎች ሚኒስቴር</u>
ለጉምሩክ ኮሚሽን
<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- <u>የኮቪድ 19 ለመከላከል የአስቸይኳ ጊዜ አዋጅ መመሪያ ቁ1/2012 ይመለከታል፤</u>

ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ሚያዚያ 10/2012 ዓ.ም በቁጥር ሚ.ም30-18/214 በተጻፈው ደብዳቤ የኮቪድ 19 ሥርጭትን ለመከላከል የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈፀም የወጣውን ደንብ ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር 1/2012 ከሚያዚያ 09 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ እንዲውል የተወሰነ መሆኑን እየገለጽን የመመሪያ ቅጂ16 ገጽ አባሪ ከዚህ ጋር የላክን መሆኑን እንገልጻለን።

"ከሠላምታ ጋር"

ነብዩ ሳሙኤል
የሚኒስትር ጽ/ቤት ተወካይ

<u>ግልባጭ፣</u>

- ለስትራቴጂክ አጋርነት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት
- ለሴቶችና ሕፃናትና ወጣቶች ዳይሬክቶሬት
- ለውስጥ ኦዲት አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለኮምኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
- የስትራቴጂክ ፕላንና ፕሮጀክት አስተ.ዳይሬክቶሬት
- ለመረጃ ቴክኖሎጂ ለማትና አስተ.ዳይሬክቶሬት
- የተቋማት ስጋት ስራ አመ/ስነ-ምግባር ዳይሬክቶሬት
- ለሚኒስትር አማካሪዎች

<u>ገቢዎች ሚኒስቴር</u>

Phone: +251 11 662 98 00/ 01/02/03/04/05/06/07/08 Fax: /+251 11 662 98 17
face book page: ministry of revenues. FBP: mor Ethiopia Twitter: erca@twitt

## <u>አባሪ አንድ</u>

## የኮረና ቫይረስን ለመከላከል እና አካላዊ እርቀት ለመጠበቅ የተዘጋጀ ጊዜያዊ የህዝብ ትራንስፖርት ተሽከርካሪዎች ጭነት ልክ መመሪያ

| ተ.ቁ | የተሽከርካሪ የስምሪት ምድብ | | | ሙሉ የመጫን የወንበር አቅም /አሽከርካሪውን ሳይጨምር | የወንበር አቅም ቅናሽ እንዲደረግ የተፈለገው | አዲስ የጭነት ልክ ገደብ በሰው ብዛት/አሽከርካሪውን ሳይጨምር | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ልዩ፣ አገር አቋራጭ፣ መካከለኛ እና አነስተኛ | | | 64 | 50% | 32 | ሁሉም የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ከአሽከርካሪው ጀርባ የሚገኘውን ወንበር ከተሳፋሪ ነጻ ማድረግ ይኖርበታል |
| | | | | 60 | 50% | 30 | |
| | | | | 54 | 50% | 27 | |
| | | | | 48 | 50% | 24 | |
| | | | | 44 | 50% | 22 | |
| | | | | 40 | 50% | 20 | |
| | | | | 31 | 51.6% | 15 | |
| | | | | 28 | 50% | 14 | |
| | | | | 24 | 50% | 12 | |
| | | | | 14 | 50% | 7 | |
| | | | | 12 | 50% | 6 | |
| | | | | 10 | 50% | 5 | |
| 1 | የከተማ አውቶቡሶች | | ፐብሊክ ባስ | 50 | 50% | 25 | |
| | | አንበሳ | መደበኛ | 42 | 50% | 21 | |
| | | | አርትኩሌትድ | 47 | 51.1% | 23 | |
| | | | ተደራራቢ/ፎቅ/ | 70 | 50% | 35 | |
| | | ሸገር | መደበኛ | 42 | 50% | 21 | |
| | | | ተደራራቢ/ፎቅ/ | 70 | 50% | 35 | |
| | | | የተማሪ /ትልቁ | 42 | 50% | 21 | |
| | | | የተማሪ ትንሹ | 31 | 51.6% | 15 | |
| | የከተማ አነስተኛ እና መካከለኛ | | ሀይገር | 27/37 | 51.9% | 13 | |
| | | | መካከለኛ /ቅጥቅጥ | | 50% | የተፈቀደው የመጫን አቅም ግማሽ (50 %) ብቻ | |
| | | | ሚኒ ባስ | 10 | 50% | 5 | |
| | ታክሲ | | ሚኒባስ | 10 | 50% | 5 | |
| | | | 7 ሲተር | 6 | 50% | 3 | |
| | | | ሴዳን/ላዳ | 4 | 50% | 2 | |
| | 3 እግር፤ | | 3 እግር | 2/5 | 50% | 1 | |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ባለሞተርና ሞተርአልባ ሳይክል እና | | ሞተር ሳይክል | 1 | | 0 | ከአሽከርካሪ ውጭ ተሳፋሪ መጫን አይቻልም |

## አባሪ ሁለት

## ጊዜያዊ የሀገር አቋራጭ ስምሪት መስመሮች እና የአውቶቢሶች መውጫ ሰዓት ላይ የተደረጉ ለውጦች

ከዚህ ቀደም መነሻቸውን አዲስ አበባ ከተማ በማድረግ በስድስት የተለያዩ መናኸሪያዎች በፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣን ይሰጥ የነበሩ የአገር አቋራጭ መስመሮች ስምሪት ላይ ወቅታዊውን ከቪድ 19 ቫይረስ ስርጭት ለመከላከል የሚያስችሉ ስራዎች በሁሉም የሀገር አቋራጭ አውቶቢስ ተርሚናሎች (መናኸሪያዎች) ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ለመስጠት ያስችል ዘንድ አገልግሎቱ ከመመሪያው የተፈጻሚነት ቀን ጀምሮ ላልተወሰነ ጊዜ በ50 በመቶ በላይ እንዲቀነስ የሚደረግ ሲሆን በተጨማሪነትም ከአዲስ አበባ ወደ ተለያዩ የሀገሪቷ ክፍሎች የተሽከርካሪዎች መነሻ ሰዓቶችም ላይ ለውጦች ይደረጋሉ ።

በዚህም መሰረት ከዚህ ቀደም በየዕለቱ በአማካኝ ስምሪት ይሰጥባቸው ከነበሩት 232 ልዩ ልዩ የሀገር አቋራጭ መስመሮች በ60 በመቶ በመቀነስ በየዕለቱ በአማካኝ እስከ 82 መስመሮች ብቻ እንዲወጡ የሚደረግ ሲሆን በተመሳሳይም ከዚህ ቀደም አብዛኛዎቹ ተሽከርካሪዎች ከተርሚናሎች ይወጡ ከነበረው ከጠዋቱ 12:00 ሰዓት ለተሻለ አፈፃፀም ያመች ዘንድ በአራት የተለያዩ ሰዓቶች ተከፋፍሎ እንዲወጡ የሚደረግ ሲሆን በዚህም መሰረት የመጀመሪያ ወጪዎች ከጠዋቱ 12:00 ላይ የዕለቱን 40 ከመቶ ተሽከርካሪዎች፤ከጠዋቱ 2:00 የዕለቱን 30 ከመቶ ተሽከርካሪዎች ፤ከጠዋቱ 4:00 ላይ የዕለቱን 20 ከመቶ ተሽከርካሪዎች ከቀኑ 6:00 ላይ በተመሳሳይ የዕለቱን 10 ከመቶ ተሽከርካሪዎች ከሀገር አቋራጭ የአውቶቢስ ተርሚናሎች የሚወጡ ይሆናል። በአጠቃላይም ከዚህ ቀደም በመደበኛ ስምሪት ይሰጥባቸው ከነበሩ 232 መስመሮች ውስጥ ለጊዜያዊነት 199 ላይ ብቻ ስምሪት የሚሰጥ ሲሆን በየዕለቱም በአማካኝ ለ82 መስመሮች ላይ ስምሪት በመስጠት ሳምንቱን ሙሉ የአገር አቋራጭ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ይሆናል ።

ዝርዝር የመስመሮች ብዛት እና መነሻ ሰዓት እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ተመላክቷል።

| ቀን | ስምሪት | የአውቶቢሶች መነሻ ሰዓት |
|---|---|---|

Federal Democratic Republic of Ethiopia
Office of ...
No 1

